# <u>ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር</u>

*ሀማ ቱማ*

*" ያሰብከው ዓላማ አልሆን ብሎ ሲከሽፍ*

*ሁኔታው ሲጠጥር*

*ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር:: "*

*ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ (ገሞራው)*

*ታዋቂው የኪነት ሰው ኃይሉ ገብረ ዮሐንስ ሀገር ወዳድ ትግሉን በአፍ መደገፍ ብቻ ሳይሆን በሕዝቡ ትግል በግንባር ቀደምነት ታግሎ ብዙ መከራን የተቀበለ ዜጋ ነው:: ታስሯል፣ ለስየል ተጋልጧል፣ ብዙ እንግልት ደርሶበታል፣ተሰዷል፣ በስደትም ብዙ መከራ ደርሶበታል:: መሬት ለአራሹ ብለው ተማሪዎች ሲታገሉ ከዩኒቨርሰቲ ከተባረሩት ዘጠኝ ተማሪዎች አንዱ ነበር:: እኔ እስከማውቀው ገሞራው የሆነ የፖለቲካ ድርጅት አባል ሆኖ አያውቅም ግን ኢሕአፓንም ሌሎች ንም ለሕዝብ የሚታገሉ ድርጅቶችን ደግፏል፣እየደገፈም ነው:: በሆነ ድርጅት ባለመግባቱ የሚ ቀርጣቸው ጥቂቶች አይደሉም:: ሁሉም ሰው በተወሰነ ቦይ ገብቶ ካልፈሰሰ አልዋጥ የሚላቸው ክፍሎች አሉና ነው:: ሰው በትግል ተሰልፎና የተደራጁትንም ደግፎ የበኩሉን አስተዋፅዖ ካደረገ በቂ መሆኑን መረዳት ይሳናቸዋል::*

*ዘንድሮ ድርጅትን በተመለከተ ውዝግብሩ በርከትከት ብሏል:: ድርጅት ለምኔ የሚሉ ብቅ ከማለ ታቸው ሌላ (የተደራጀው ወያኔ ምንኛ ደስ ይለው!) ድርጅትን ደግሞ በእስር ቤት ፈርጀው አባሉ የማይተነፍስ ፍጡር ነው ሊሉን የሚቃጡም ተደምጠዋል:: በዚህም መሰረት የግለሰብ ነፃነ ትና የድርጅት ማዕከላዊነት ወይም ስነ ስርዓት ህግ ደብለቅለቅ ያለባቸው አሉ:: የድርጅት አባላ ት በመሰረቱ የድርጅታቸውን አቅዋም ማንፀባረቅና መሰረታዊ መርሁን ማስተጋባት አለባቸው:: ከዚህ ሌላ ግን የማንም ድርጅት አባላት ማንነታቸውና ግለሰባዊ ስምሪታቸው ያለና የሚከበርም ነው:: የድርጅት አባል የሆነ ጓድ ሐዋርያ የሚል የራሱን መፅሔት ማውጣት ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ድርጅቱ እንዲቆጣጠረውና የሆኑ ፅሁፎችንም እንዲያግድ የጠየቁ ብዙዎች ነበሩ:: የድር ጅት አባል ቢሆንም አዘጋጁ የሚያትመው ጋዜጣ የድርጅት አለመሆኑን መረዳት ተስኖአቸው ቆይቷል:: ነፃ ፕሬስ ይኑር ይከበር እያሉ ግን መፅሔት/ጋዜጣ ላይ ማዕቀብ መደገፋቸውም ጥፋቱ አልታያቸውም:: በአሁኑ ጊዜም አንዳንድ ራሳቸውን የቻሉ ግን ለድርጅቱ ቀና አስተያያትና ድጋፍ ያላቸው ድረ ገፆችን ድርጅቱ ተቆጣጥሮ የሚያካሂድ የመሰላቸው ተመሳሳይ ስህተትን ይፈፅማሉ:: በነዚህ መድረክ የወጣው የቀረበው ሁሉ የድርጅቱ ነው ብለው በዚያው ወቀሳና ክስ ይደረድራሉ:: ይህ ፀሀፊ ራሱም በብዕር ስምና በግል የሚፅፋቸው ትችቶች ሆኑ ልብ ወለዶች ና ግጥሞች ራሱን እንጂ ድርጅትን የሚወክሉ አለመሆናቸውንም መረዳት ይሳናቸዋል:: የቁሳርን*

ለቄሳር ቢታወስ ባማረ! ሌሎች ደግሞ ያወቁ የነቁ መስሏቸው ግን በመሰረቱ የድርጅት አባላትን ተሳትፎ ለማገድ የድርጅት አባላት የብዙሀን ድርጅቶች አባላት ወይ ኮሚቴ አባል አይሁኑ ይላሉ ነገር እንዲጠፋ ዳኛውን ግደል ዓይነት ነው--የነቃው ቦታ ለቆ ባሰኘን እኛ እንጨፍር ነው ነገሩ።

ወደ ቁምነገሩ ለመመለስ። እንዲላላ የሚፈለገው ጠጣር ወያኔ ነው። ጠጣርነት ደግሞ አንፃራዊ ነው። የወያኔ ጠጣርነት ከሕዝብ ትግልና ከተቃዋሚዎች ደካማነት፤ልፍስፍነት፤ መላላት የሚሰርፅ ነው። የወያኔ አገዛዝ የወረቀት ነብርነት መሰረታዊ ቢሆንም ከደከመ ተቃዋሚ አንፃር ሲታይ ግን የጠነከረ መስሎ መታየቱ የሚካድ አይደለም። በእርግጥ አሜሪካ ኃያል መንግሥት ነውና ወገባችን ይሰበርለት እንፀልይለት የሚሉት ወያኔ ጠንካራ ነውና እንበርከክ ማለታቸው የሚጠበቅ ነው። ዛሬ የቆሸሸ ታሪካቸውን በግርግር ሊያድሱ የሚሞክሩ ግለሰቦቸ ትላንት እየተገዙ መታገል በሚል የቡከን ፊሊፕ ለወያኔ መጎንበስን ሰብከው እንደነበር የምንረሳው አይደለም። ተንበርክኮ ትግል ደግሞ እያንቀላፉ ተኩስ ዓይነት ነው--ቀልድ። ከዚህ ባሻገር ግን የወያኔ ጥንካሬ ዛሬም ቢሆን የእንቧይ ካብ ነው። ሆኖም ከትግል አንፃር ሲገመገም ደግሞ ይህ አገዛዝ ምንም ቢዳከምም ፤ ምንም ውስጡ ከመ ወንፊት እየሆነ ቢመጣም መንግስታዊ መዋቅርንና ማዕከልን በመያዙ አንፃ ራዊ ጥንካሬ ያለው መሆኑ መዘንጋት የለበትም። የመንግሥት ስልጣን በእጁ ነውና፤ የሀገሪቷ ገን ዘብ በቁጥጥሩ ነውና (ያውም ወርቁንም በጠራራ ፀሐይ እየሰረቀ ያለ ወሮበላ ቡድን ነው!)፤ የሚያዘው የጦርና የአፈና ኃይል አለውና ጠጣር ነው። የት ላይ ለሰላሳና ደካማ ጎን እንዳለው ማወቅ ደግሞ የሚታገሉ ክፍሎች ቀዳሚ ስራ መሆን ያለበት ነው። የተጠላ አገዛዝ ነው ቢባልም በገንዘብና በማስፈራሪያ የገዛው " ድጋፍ" እንዳለው መሳት የለበትም። በጥቅሉ ሁሉም የትግራይ ተወላጅ ወይኗል ማለት ትክክል ባይሆንም የማይናቀው ቁጥር ግን የወያኔ መወገድ በትግራይ ተወላጆች ላይ መዓት ያመጣል የሚለውን የወያኔ ቅስቀሳ ተቀብሎ ለእነ መለስ ማመቸቱ ግልፅ ነው። የወያኔ ጠንካራ ጎኑ (ድክመቱንም ያቀፈው) ሕዝብን በጎጥ፤በብሄረሰብና በሀይማኖት ለመከ ፋፈል መቻሉ ነው። በፈለገው ደረጃ ይህ መሰሪ ዓላማው ባይሳካለትም ጉዳት እያደረሰ ለመሆኑ ምንም ጥርጥር የለውም። በሌላው ገፅ ግን ይህ ፖለቲካው ደግሞ አብዛኛው ሕዝብ -ፀረ ወያኔ እንዲሆን ማድረጉ የአገዛዙ መሰረታዊ ድክመት ነው። አብዛኛውን አደራጅቶና አስተባብሮ በአገዛዙ ላይ ማሰለፍ-ማታገል ገና መሰራት ያለበት መሆኑ እንዳለ ሆኖ።

ለወያኔ አንፃራዊ ጠጣርነት የረዳው ሌላ ኃይል ባዕዱ ነው--በተለይም አሜሪካ። ይህን ፀረ ሕዝብ ቡድን ለስልጣን ያበቃው አሜሪካ የራሱን ብሔራዊ ጥቅም ሲያሳድድ የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም ረግጧል፤ጎድቷል። የጎረቤት ሀገሮች--በተለይ ሱዳን-- ደግሞ ከወያኔ አገዛዝ ጋር የጠበቀ ግንኙነት በመመስረታቸውና ለታጋይ ኃይሎች ዝግ መሆናቸው ለወያኔ ረድቶታል። ይህ ሁኔታ ም በግልባጩ ለወያኔ ድክመት በር ከፋችነቱም እየታየ ያለ ነው። የአሜሪካንን ትዕዛዝ ለማስፈፀ ም ወደ ሶማሊያ ጦር በመላኩ በቀላሉ ሊወጣ ከማይችልበት ቀውስ ውስጥ ገብቷል። ጦሩ ውስጥ

ጉምጉምታና ችግር ተባብሷል:: ሱዳንን ጠቀምኩ አግባባሁ ብሎ የሀገርን መሬት አሳልፎ በመስጠ ቱም የሕዝብን ቁጣ አትርፏል:: በኦጋዴንም ያለው ጦርነት የወያኔን አረመኔነት ከማሳየቱ ሌላ ለወያኔና አልፎም በረጅሙ ለኢትዮጵያ ችግር ፈጣሪ ነው:: ሰሜን በድንበር ያለው ሁኔታ ሌላ ጦርነት ያቀበቀበ መሆኑ እንዳለ ሆኖ ወያኔ የሚበጁትን የሻዕቢያ ተቃዋሚዎች ይዞ ለድል ከበቃ የትግራይ ትግሪኚ ህልሙን ዳግም ሊያድስ መጣሩ የማይቀር ነው:: ያለው ተጨባጭ መረጃ የመለስ ቡድን ውሎ አድሮ ትግራይን ለመገንጠል መወሰኑን ግልፅ ያደርጋል:: ስብሐት ነጋ ሽንፈት ከመጣብን ሀገሪቷን በታትነን እንሄዳለን በሚል ሲደነፋ ተደጋግሞ ተደምጧል:: ለአሜሪካ ታዛዥ በመሆን የዋሽንገተንን ድጋፍ አግኝቶ ለመጠናከር ቢነሳም በሌላ በኩል ደግሞ የሶማሊያ ወረራው ወደ ባሰ ቀውስ ከቶ እየጎዳው መሆኑ ይታያል:: ባለው የአካባቢ ሁኔታም የወያኔና የሱዳን ግንኙነት በጥያቄ ሊገባ የሚችልበት ሁኔታ ከመኖሩ በላይ የተወሰኑ አረብ ሀገሮ ችና ሻዕቢያ የሶማሊያውን ሁኔታ በመጠቀም የወያኔን ቀውስ ለማባባስ በመሯሯጥ ላይ ናቸው:: በሶማሊያም አክራሪ ክፍሎች -- በአፍጋኒስታን እንደ  ታሊባኖቹ-- ዳግም እያየሉ ከመምጣታቸ ው ሌላ በዚያድ ባሬ የባህር ኃይል አዛዥ በአድሚራል መሀመድ ኦስማን የሚመራውም የኦጋዴን ነፃ አውጪ ግንባር የሚጠናከርበት ሁኔታ ተመቻችቷል:: ለነገይቷ ኢትዮጵያ በዚህም በዚያም የግንጠላ ፈንጂ እየቀበረ ያለው ወያኔ በተከፋፈለ የሕዝብ ትግል ሁኔታ እየመረቀነ ያለ መሆኑ ግልፅ ነው:: ይህን ሁኔታ ለሽንፈቱ መጠቀም ይቻላል ቢባልም ተቃዋሚ ድርጅቶች ሊጠቀሙበ ት ይችላሉ ወይ የሚለው ጥያቄ ግን እስካሁን መልስ ያገኘ አይደለም::

የወያኔ ጠጣርነት ከመደራጀቱም ጋር የተያያዘ ነው:: ድርጅት ሆኖ ታግሎ ለስልጣን በመብቃቱ ም የድርጅት ካድሬዎች፣ ጦር ወዘተ አለው:: ጠበቅ ያለ አሰራር፣ ሙያተኛ አሰራር አለው:: ስልጣን ያበላሻልና ዛሬ ዘረክረክ ብሎ ሲታይም ተፃረው ከቆሙት ኃይሎች አንፃር ድርጅታዊ ይዘቱ አሁንም ጠንካራ ነው ቢባል ስህተት አይሆንም:: ተቃዋሚ ኃይሎችን በመከፋፈልም ተጠናክሯል:: ይህ የተቃዋሚ ኃይሎች ድክመት ነው በሌላ በኩል:: ወያኔ የትግል ተመክሮ አለው--ይህ ጠጣር ያደርገዋል፣ በተለይም የትግል መስክ ማንም ዘው ብሎ በመሪነት የሚፈነጭ በት የመሰላቸው በዝተው ባሉበት ሁኔታ:: ወያኔ ለውጭ ዲፕሎማቶቹ ባወጣው የ 52 ገፅ ማዘዣ ወይም መመሪያ መሰረትም እየተሰራ ስለሆነ ወያኔ በሙሉ ደረጃ ባይሆንም ውጤትን አግኝቷል:: ድርጅቶችን መከፋፈል--እውን ሆኗል:: የተቃዋሚ ድርጅት “ አክራሪ ” መሪዎች ላይ የሚያጥላ ላ ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ-- ለወያኔ ባደሩና በተደናገሩ ሁሉ እየተሰራ ነው:: በባዕድ ያለውን ኢትዮ ጵያዊ መከፋፈል-- ይህም በሚገባ ተከናውኗል፣ የአንድነት ኃይሎችን ማጋጨቱ ላይ ብዙዎች ተሰማርተዋል፣ ተቃዋሚውን መሳቂያ የሚያደርጉ አስመሳይ ፖለቲከኞች መድረክ ይዘዋል፣ የትግል ታሪክና የሕዝብ ሰማዕትን ማንቋሸሹ በዝቷል፣ ወዘተ ወዘተ... በሰርጎ ገቦችና ያወቁ በመሰ ላቸው ግን ባያውቁትም ከበስተጀርባ በወያኔ ቅጥረኞች በሚነዱ ግለሰቦችና እወቁን ባይ ግብዞች፣ የብልሹ ታሪክ ባለቤቶች በሆኑ ፀረ ንስሀ ግለሰቦች እየተካሄደ ያለው ከፋፋይና አተራማሽ ድርጊ ትና ዘመቻ ሁሉ ለወያኔ ጠቅሞ ጥንካሬን ለግሶታል::

ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥር  በተባለው መሰረት  የላላውንና መወጠር ያለበትን ማወቁ አስፈላጊ ነው፡፡ ይህን ለማድረግ ደግሞ ያለን ድክመት ማወቅና ለማረም መጣር አስፈላጊ ይሆናል፡፡ ለሞኝ ጉድጓድ አያሳዩትም ቤት ነው ብሎ ይገባበታል የተባለውን በሚያስታውስ ደረጃ ድርጅቶች ከዚህ  በፊት የነበራቸው ድክመት በተጠቀሰ ሊደግሙት የሚቸኩሉ መብዛታቸው አስገራሚ መሆኑ አልቀረም፡፡ በመሆኑም የትግል ታሪክን በሚገባ በማወቅና ሰማዕትንም በመዘከር ፈንታ ያለፈውን ማውገዙና በጭፍን መጨፍጨፉን የመረጡ አሉ፡፡ በዚህም ራሳቸውን ለትዝብት አጋልጠው ትግሉን ጎድተዋል፡፡ የቀውሱ ሁኔታ ለለውጥ ያመች ዘንድ በሕዝብ ጎራ ያለውን ድክመት ልናስወግድ ማለትም የላላውን ልንወጥር ስንነሳ በቅድሚያ ሕዝብን በተመለከተ የሚነገ ሩ ወይም የተያዙ የተሳሳቱ ግንዛቤዎችን ማረም እንገደዳለን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጫኑትን ቢጭኑት የሚችልና ለመብቱ ከቶም የማይታገል ሆኗል የሚሉ አሉ፡፡  ሕዝብ ይቀየርልን ሊሉ ጥቂት የቀራቸው እነዚህ ይህን የሚተቹትን ሕዝብ ለማታገል እምብዛም የለፉና የጣሩ ክፍሎች አለመሆናቸውንም መጥቀሱ አስፈላጊ ነው፡፡ ሌሎች ደግሞ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጨዋ ነውና (ኢትዮጵያዊ ጨዋነት ይሉታል) በገዢዎቹም ላይ ማመፁን ወይም ብረት ማንሳቱን እንደ ብልግና ሊቆጥሩበት ተነስተዋል፡፡ ህግ አራዊት ይሉት የነበረውን ሕገ መንግስት ብለው ተቀብለው / ተቀበሉ / እያሉ  ብረት ያነሳውን ሁሉ በፀረ ዴሞክራሲነት ሊያወግዙ / ባይቀስሱም ሊገዝቱ/ የተነሱት የለመደባቸው ፕሮፌሰር ምሳሌ ናቸው፡፡ ሕዝብን ከትግል የሚያርቅ ወይም የሚያግድ ጨዋነት የለም፤ ሊኖርም አይጠበቅም፡፡ ሰብዕናን አለማስከበ ር፤ መብትን አለመጠየቅ ነው ብልግናና ውርደት ብንል ተገቢ ነው፡፡ ለሙሶሊኒ፤ለግራዚያኒ፤ ለወዲ ዜናዊ ጨዋነት ወይ ርህራሄ አልነበረም፤ ሊኖርም አይገባም፡፡ በጠላት ላይ መጨከን እንጂ መለስለስ የትም አያደርስም--ጠላት በጥርስ ሲገኝ እባክህ አታስጎምጀኝ ነው ቁም ነገሩ፡፡ ሀገር እያጠፋ ላለ አረመኔ ወያኔ ጨዋ ወይም ቻይ መሆኑ ሀገርን ይጎዳል፡፡  ስለዚህ ሕዝብን ጨዋ ነህ አትታገል ብሎ ሰበካው ወይ ላለመታገል ይህን ዓይነት ማጠየቂያ መስጠቱ የሚበጅ አይደለም፡፡ በሌላ በኩል በእርግጥ ሕዝብ ሆ ብሎ እንዲነሳና ይህ ፀረ ሕዝብ አገዛዝ እንዲወገድ የሁሉም ጤነኛ ዜጋ ፍላጎት ቢሆንም ይህ ባለመከሰቱ ወደ ቀቢፀ ተስፋ ሊከት መቻሉን መገመት እንችላለን፡፡  ሕዝብ ግን የሚመራውና የሚያታግለው ባገኘበት መነሳቱና አስፈላጊውንም መስዋ ዕትነት መክፈሉን ደግመን ደጋግመን ያያነው ነው፡፡ በ97 ምርጫም ጊዜ ታይቷል፡፡ ድክመቱ ከሕዝብ ሳይሆን ከሌላ ነው፡፡ ድርጅቶች የራሳቸውን ድክመት ማስወገድ መቻል አለባቸው ማለት ነው፡፡ ባውዛው ወደ ራስ፤ወደ ውስጥ፡፡

ድክምቱ ያለው ወይም መላላቱ የተከሰተው ከተቃዋሚዎች ጎራ መሆኑ  የሚታወቅ ነው፡፡ ብዙዎ ች ድርጅቶች ባለመተባበራቸው ነው ይላሉ፡፡ ችግሩ ግን ከዚህ ባሻገር ነው፡፡ በበኩሌ ሕዝብ ተባበ ሩ ወይም ተሰባበሩ ብሏል የሚለውን የት ቦታ መቼ ብዬ ከመጠየቅ ባልቆጠብም ይህን መደጋገም ይወድ የነበረው ዶክተር እገሌ ደግሞ ተሰባብሮ ፓርላማ ገብቶ ለወያኔ መደፋቱን ለመታዘብ

በቅተናል። ድር ቢያብር አንበሳ ያስር የሚባለው እንዳለ ሆኖ ድርጅቶች ህብረት መሰረቱ አልመ ሰረቱ በየራሳቸውም ተጠናክረው የትግል ትብብር በገቢር ቢኖራቸው ውጤቱ ያምር ነበር። በ97 ለምሳሌ ቅንጅትና ህብረት ባይተሳሰሩም የሚሄዱበት አቅጣጫ ስለተመሳሳለ ሕዝብን በመቀስቀስ ና በማሰለፍ ደረጃ ውጤት ሊገኝ ተችሏል። አካሄዳቸው ደግሞ ሲፈራቀቅና ተፃራሪም ሲሆን ያው ጉዳትና ድክመት ሊከተል ችሏል። ማንኛውም ድርጅት ሰፊውን ሕዝብ የሚያሰባስብ ፖለቲ ካና መስመር ይዞ ከተነሳ ሊጠናከር መቻሉ ግልፅ ነው። በዚህ አንፃር የድርጅቶች ድክመት ማበር አለመቻላቸው ሳይሆን እርሰ በርስ መጠላለፋቸው ነው። በአዲስ የሚፈጠሩት ድርጀቶች ቀደም ብለው ሲታገሉ የነበሩትን ካላጠቁ የማደግ መንገዱ ዝግ የሆነ ይመስል በጣውንትነት ይሰማራሉ። የተጠቁትም ሲከላከሉ በሚፈጠረው ግርግር ሌባው ወያኔ ያመቸዋልና ሰርጎ ገብቶ ያናክሳል።ድርጅቶች በተለመደው መንገድ የየራሳቸውን መርሀ ግብር ወይም ፕሮግራም በአጭሩ ም በስፋትም ቢያቀርቡም ይህንኑ በስራ ከማዋል አንፃር በሚገባ የተጤነ ዘዴና ስልት መያዝ ባለመቻላቸው አካሄዳቸው ግብታዊና የጀማሪ/የአላዋቂ ሆኖ ቢያንስ በተንኮልና በድርጅታዊ አሰራር ሰልጠን ላለው ወያኔ ሰለባ ሆነው ይገኛሉ። የፖለቲካ ድንግሎችም ወላዷን ምጥ ሊያስተ ምሩ ሲዳክሩ ነገር ዓለሙ መያዣ መጨበጫ አጣና ሁሉም ግራ ተጋባ።

ይህን ከማረም አንፃር ደግሞ “ተጠንቀቅ ወደል እንዳትገባ ገደል” የሚሉና ጎበዝ “ቢከፍቱት ተልባ” ከመሆን ያድነን የሚሉ ባለመወደዳቸው የተሳሳቱ ሊታረሙ ቀርቶ ተሳሳቱ የሚላቸው እየተወገዘ እነሱም ተገብዘው እንዲቀጥሉ በር በመከፈቱ ችግሩ ተባብሷል። ድርጅቶች ሆኑ መሪ ዎቻቸው በመሰረቱ የሕዝብ አገልጋይ መሆን ሲገባቸው ራሳቸውን ከሕዝብ በላይ በማድረግና ከወቀሳና ሂስውጪ ነን በማለታቸው የእርምቱ ሙከራ ፍሬ አልባ ሆኖ ቆይቷል። አንቱ የተባሉት ግን ውሎ ሳያድር ትግሉንም ሕዝብንም እያጋለጡና አልፎም ለወያኔ እያደሩ መምጣታቸውን በምፀት መቀበል ተገደናል። ትግሉም አፍ ያለው ያግባሽ ዓይነት ሁኔታ መጥቶበት በአፋቸው ጥሬ በሚቆሉ ተይዞ፣ አወቅን ልሂቅ ሆንን ላሉ ተጋልጦ ወኔውም ፅናቱም የሌላቸው ሆዳሞች ሊያጨናግፉት ቻሉ። የሙት ከተማ አድማን ያስታውሷል። ይህንና መሰል ትችቶችንም ማቅረቡ ለገንቢ እርማት መሰረት ሆኖ ሳለ በአፍ እላፊና ክብረነክ በወመሰዱ ውዳሴ ከንቱ አሸንፎ፣ የሞኝ ምስጋና የግንቦት ደመና መሆኑ ተረስቶ፣ የመንደር ማንዴላዎች ተበራክተው የሕዝብም መስዋዕ ትነት ተገቢውን ድል አጣ። ላላንና ወያኔን አጠጠርን። ከፅንፍ ፅንፍ መስፈንጠሩም የመደናገራች ንና ቀቢፀ ተስፋችን ነፀብራቅ ሆኖ ግራ ቀኝ ስንላተምና ጠላትን በወዳጅ፣ ወዳጅን በጠላት ፈርጀ ን ስንሰለፍ ወያኔ ቁስሉን ልሶ ሊያገግም የሚችልበትን ሁኔታ ፈጠርን ማለትም እንችላለን። አንዳንድ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ቆመናል የሚሉ ቡድኖች ወያኔን ሳያወግዙ የወያኔ ጠላት የሆነ / የሆኑ ድርጅቶች ላይ ግን ነጋ ጠባ ሲረባረቡ ስናይ የችግሩን ሚዛን ክብደት እንረዳለን።

ሂስ ወይም ትችት ገንቢም አፍራሽም ሊሆን ይችላል:: አትንኩን የሹም ዶሮ ነን ባዮቹን ወደ ጎን እንተውና ሂሰ በተገቢው መንገድ በገንቢ መንፈስ ሊቀርብ ካልቻለ አፍራሽ ሊሆን ይችላል:: አንድ የልብስ መስፊያ መርፌን የሰበረ ሰው የዓለምን አብዮት አደናቀፈ እስከማለቱም ሊያደርስ ይችላል:: ልክ ሊኖረው ይገባል:: ዘለፋና ማንቋሸሽን የራቀ መሆን አለበት:: ስህተትን ለማረም እንጂ የተሳሳተውን ለመጉዳት መሆን የለበትም:: ከሁሉም በፊትና በላይ ደግሞ ሂስ ወይም ወቀሳ በአሉባልታና በምናልባት ላይ ተመስርቶ የሚቀርብ ሳይሆን ሀቅን መሰረት መነሻ ያደረገ መሆን አለበት:: በአሁኑ ጊዜ በድርጅቶችና በመሪዎች ላይ እየቀረበ ያለው በረከት ያለው ሂስ ወይም ትችትና ወቀሳ አፍራሽና በሀቅ ላይ ያልተመሰረተ ነው:: የግለሰቦችን ስም ማጥፋትና የተከፈለን መስዋዕትነት ማርከስ ማክቸልቸሉ ቅድሚያን ይዟል:: በ 97 ምርጫና በተከተለውም ፍጅት የተነ ሳ የነበሩ ድርጅቶችን በሰላ ሂሰ ጥፋተኛ አድርጎ መጥረቡም ብዙ አይጠቅምም--የተሳሳቱትን በማረም መንፈስ ማቅረብ ተገቢ ቢሆንም:: ይህ በድርጅቶች ላይ የሚደረግ አፍራሽ ዘመቻ ራሱ መታረም መቆም አለበት:: ካልታረመ ለወያኔ ለም መሬትን ያቀርብና ትግልን ጎጂ ዘመቻቸው ያብባል:: የወያኔ መመሪያ ሀገር ወዳድ ድርጅቶችንና ፀረ ወያኔ መሪዎችን በትኩረት በሁሉም መንገድ ማጥቃት፣ ስም ማጥፋትና ከሕዝብ መነጠል የሚል ነው:: ይህን ለማድረግ ወያኔ በቅጥረ ኞቹም በሞኞችም እየተጠቀመ ያለ መሆኑ ዛሬ የሚታወቅ ነው:: ወያኔን ትተው በታጋይ ድርጅ ቶችና በትግል ታሪክ ላይ አፀያፊ ዘመቻ እያካሄዱ ያሉትን ማወቅና በጋራ ከመድረክ ማስወጣቱ መሰራት ያለበት ነው:: ድርጅቶችንና መሪዎችን የመተቸት መብታችን የተጠበቅ ሆኖ ሳለ ገንቢ መንፈስን እንጂ አፍራሽነትን ማንፀባረቅ የለብንም ማለት ነው:: ይህ ለበታኞችና ለተክለ ሰብ አቀንቃኞቸ ባይጥምም መያዝ ያለብን አቅዋምና ልምድ ነው::

ድርጅቶች  በተጠበቀው የጥንካሬ ደረጃ ባለመገኘታቸው ያለው ቅሬታ እንዳለ ሆኖ ድርጅቶች ሌላው ድክመታቸው በጠላት ላይ ግልፅ ግንዛቤ ይዘው ወዳጅና ጠላትን ሳያምታቱ ተገቢውን ስልት ይዘው መታገል አለመቻላቸው ነው:: ወያኔ ወዳጃችን ነው የሚለው በሕዝብ ጎራ ሊደመጥ አይገባም:: ሊወጋ የመጣ ጌታዬ ቢሉት አይመለስምን ማስታወስ ያስፈልጋል:: ከ 97ኡ ምርጫ ወዲህ ደግሞ መሰረታዊ ለውጥ ሳይደረግ ( ምርጫ ህጉንና የምርጫ ኮሚሽኑን ይዘተ በተመለከተ) በወያኔ ምርጫ መሳተፍ ፍሬ ቢስ መሆኑን አለማወቅም ስህተት ነው:: ይህን ካልን በኋላ ግን ድርጅቶች በሚያምኑበትና ያዋጣናል ባሉት መንጎዳቸው መብታቸው ነው:: ችግሩ ግን ህዝባዊ በሉን ሲሉና አልፎም እነሱ በማይፈልጉት መንገድ የሚታገሉትን ማውገዝ ሲጀምሩ ነው:: ቀደም  ሲል ሰላማዊና የትጥቅ በሚል የቻይና ግንብ ከመሀል ደንቅረው አንዱን ከሌላው በማቃረን ሊፈርጁ ከተነሱት ጋር ያለንን ልዩነት የገለጥን ብዙዎች ነን:: ለነገሩ ዘላለማዊ ሰላም ዕድሜው እስከ መጀመሪያው ግጭት ነው ተብሏል ወይም ግብፆች እንደሚሉት ጠላትነት መጀመሪያ ሳያከትም ሰላም አይገኝም ማለትም እንችላላን:: ጠላት ቢያረጅ መች ወዳጅ ይሆናል? ሰላማዊ ትግል ያሉትም ይህንን በተግባር ከዋለ ዕልህ አስጨራሽ ትግል ሲያካሂዱ ካለማየታችን ሌላ ሕዝባዊ አመፅን በተመለከተ ምን ማለትም እንደሆነ በተደጋጋሚና በዝርዝር ተገልፆ ነበር::

አልፎም የትጥቅ ትግል ደግሞ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ አስፈላጊ ከሆነ ውሎ ያደረ በመሆኑ በሰላማዊው ትግል ወይም በሕዝብ አመፅ የሚታገዝ እንጂ የሚዳከም አለመሆኑን፣ የብረት ትግሉ መካሄዱ ሌላውንም የማያዳክም መሆኑንም ለማስረዳት የበኩላችንን ጥረናል:: ዛሬም ያለን እምነት ነው:: በዚህ ላይ የጠፋው ግልፅ ግንዛቤ ለተቃዋሚ ድርጅቶች ድክመት አስተዋፅዖ አድርጓል:: ይህ ሌላሊታረም የሚገባው ስህተት ነው::

ሀቁ ይነገር ከተባለም ኢትዮጵያ በደፈናው የኢትዮጵያዊ ሁሉ የእኩል ሀገር ሆና አታውቅም:: ገዢና ተገዢ፣ ጨቋኝና ተጨቋኝ፣ ባላባትና ጢሰኛ፣ ወዘተ የነበረባትና አሁንም ያሉባት ሀገር ናት:: የጥንቲቷ ኢትዮጵያዊ የምድር ገነት አልነበረችም፣የዛሬይቷም አይደለችም:: ለብዙሃኑ:: የዛሬውን አያርገውና የኦነጉ ኢብሳ ጉተማ ተማሪ ሳለ በ1957 ዓ/ም. በፃፈው ኢትዮጵያዊው ማነው? ግጥሙ የዚህን ቁም ነገር ጠቀስ አደርጎት ነበር::

" ..እናንተ ወጣቶች ኢትዮጵያዊው ማነው?
ከሆዱ ያበጠ ቦርጫም መኮንን ነው
ወይስ ኮሰስ ያለ መናጢ ድሀ ነው
ላቡን አንጠፍጥፎ ከመሬት ተታግሎ
ካገኘውም ሰብል ለጌቶች አካፍሎ
ለራሱ ከእጅ ወደ አፍ የሚያስቀረው ነው
በሉ እስቲ ንገሩኝ ኢትዮጵያዊ ማነው?
.....የሶስት ሺ ዓመት ዕድሜ ከመቁጠር
ኑ ካሁን ጀምሮ እንተባባር
አንዱ ካንዱ ልብለጥ ማለቱን ይተው
አንዱ አንዱን ልግፈፍ ማለቱን ይርሳው
የለየውን ገደል ተባብሮ ይሙላው
ያሰረውንም ገመድ አንድነት ይፍታው
ያኔ ብቻ ይሆናል መለስ የማገኘው" ::

ብሎ ነበር:: ዛሬ ወደ ኋላ ተመልሰው ኢትዮጵያዊነትን ከአስከፊ ስርዓቶችና ዘመናት ጋር በማጣበቅ ሊተረጉሙ ለሚፈልጉ ትምህርታዊ መሆን በቻለ ነበር:: ዛሬም ቢሆን ብዙሃኑ መከራውን ፍዳውን ሲያይ ወያኔና መሰሎቹ አልፎላቸዋል፣ተንደላቀዋል፣ በሕዝብ እየቀለዱ በመኖር ላይ ናቸው:: የወደፊቷ ኢትዮጵያ እነዚህን የምትጠቀልል ልትሆን አትችልም:: በምን ዓይነት? የወያኔ ቡድን ጠላታችን ነው ስንልም ጭፍን ጥላቻ ሳይሆን የሀገራችን ስርየት በግድ የወያኔን መውደቅ መንኮታኮት ስለሚጠይቅ ነው:: በወያኔ ላይ መቁረጥ የሚያስፈልገው ለዚህ ነው:: ተስፋ ያልቆረጠ መነኩሴ ምንና ሲሄድ ሴቲቱን ይሰናበታል እንዳይሆን ማለት ነው:: ያላላን አንዱ ምክንያት በወያኔ አገዛዝ ላይ መቁረጥ አለመቻላችን ነው ቢባል ተቃዋሚ ድርጅቶች ሁሉ አሌ ሊሉት የሚችሉ ሀቅ አይደለም:: ከወያኔ መተቃቀፍ ይቻላል የሚሉ ከየድርጅቱ እየተገነጠሉና በአንጃነትም እየተሰለፉ ድርጅቶችን ለማዳከሙ ስራ መጥቀማቸውም ያየነው ነው::

ለክፍፍሉ ወያኔን መውቀስ አይገባም--ጠላቶቹን መክፈል ማዳከም ስራው ነውና ለምን ስራህን ሰራህ ማለቱ አግባብ አይኖረውም:: ለድርጅቶች መከፋፈል ወይ በአንጃ መጠቃት ተጠያቂ ድር ጅቶች ራሳቸው ናቸው--ድክመቱ ውስጣዊ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ክፍፍል ሁሌም ጎጂ ሳይሆ ን አብሮ መሄድ ባልተቻለበት፤ ሊታገሉ የሚፈልጉ ከማያታግሉ ሲለዩ ውጤቱ ጥሩ ሊሆንም ይችላል:: ባቄላ ጠፋ ቢሉት.....ቀለለ አለ እንደተባለው::ሌላ ገጣሚ ደግሞ ግልግሉን ከኮሶ መሻር ጋርም አስመስሎ አቅርቦታል:: ህብረት ተባለ ቅንጅት ወይም ትብብር መሰረቱ የፀና ካልሆነ ጠቀሜታው ብዙ ላለመሆኑ በቂ ተመክሮ አለን:: በደፈናው ግን ድርጅቶች መከፋፈላቸ ው ካዳከማቸው ለመላላታቸው ሌላ ምክንያትና ነፅብራቅ ሆኗል ቢባል ስህተት አይሆንም:: ቀደም ብሎ ለማቅረብ እንደተሞከረው ግን ድርጅቶች በግድ ህብረት መመስረት ባይኖርባቸውም ለኢትዮጵያ በሀቅ የሚታገሉት መተባበር ቢችሉ ማለትም ቢረዳዱ ና አይዞን ቢባባሉ ጠቃሚ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ የወያኔን አገዛዝ መውደም ይፈልጋል:: "ትግል በፀሎት" እያሉ ከሰማይ ጋር ሊያጣሉን የሚሞክሩ ባይጠፉም ወያኔ በምለላ ብቻ የሚጠፋ አይደለምና ትግል መኖሩ የግድ ነው:: ተፀለየ አልተፀለየ ከባዶ ሌማት መመገብ አይቻልም:: ራሳቸውን የሚረዱትን ፈጣሪያቸው ይረዳቸዋል የሚለው ጥቅስ በመፅሐፍ ቅዱስ ባይገኝም፤ የፈጠራቸው ለተበደሉት ታዳጊ ይሆናቸ ዋል  ቢባልም አምላክ ላሞቼን ይጠብቅልኛል ብሎ  የበረትን በር ክፍት መተዉ የባለቤቱ ጥፋት መሆኑን እናውቃለን:: ማለትም ራሳችንን መርዳትና ነፃነታችንን ለማስመለስ መታገል አለብን ማለት ነው:: በጣሊያን ወረራ ጊዜም የተደረገው ይህ ነው:: ስለዚህም ወያኔን መታገል ያስፈልጋ ል:: መለመን መለማመጥና የሌለውን ርህራሄ ያሳይ ዘንድ ተዓምር መጠበቅ ሳይሆን በትግል ግብግብ መግጠም፤ መድማት ማድማት፤ መሰዋት መግደል፤በፅኑ ትግል ማንበርከክና ማስወገድ ያስፈልጋል:: ይህን የትግል ሀ ሁ መደጋገም ማስፈለጉ ለምን እየላላን እንደመጣን ጠቋሚ ነው:: ትግል ስንልም በወያኔ ዕቅድ መሰረት በፈለገን መጓዝ ሊሆን አይችልም:: በየወቅቱ ወያኔ አዳዲስ መፈክር እየለገሰ የትግላችንን ትኩረት ማስቀየር መቻሉ ሌላ ድክመታችን ነው:: የሕዝብን ድምፅ ነጥቆ በህገ ወጥ ስልጣን ይዞ ባለበት የሕዝብ ድምፅ ይከበር በማለት ፈንታ የታሰሩት ይፈቱ የሚል መፈክር አሸከመን:: ዛሬም ዋናው ግብና መፈክር የወያኔ አገዛዝ በትግላችን ይውደ ም መሆን ሲገባው ደንቃራ መፈክሮችን እያሸከመን አልፎም ተቃዋሚ ኃይሎችን መሳቂያ መሳለ ቂያ የሚያደርጉ እርምጃዎችንም ሊያስወስድ እየገፋፋ አለ :: ዱላ ስንል መላ የሚል ንትርክ ያስ ከፍትብናል:: ትጥቅ ትግል ስንል ወኔውም ቁርጠኛነቱም የሌላቸው በዚሁ ትግል ስም እንዲያሾ ፉ ይገፋፋብናል፤ የታጋዮቾ ህብረት ስንል የምርጫ ተሳታፊዎች መድረክ እነሆ ያሰኛል:: ይህ መቆም ያለበት ነው:: መካሄድ ያለበት ሁለገብ ትግል ሲሆን በዚህ ወያኔን በማስወገድ መርሀ ግብር በተቃኘ ትግል ውስጥ ሕዝባዊ አመፅና ትጥቅ ትግል በስልት ተቀናጅተውና ተደጋግፈው ሊካሄዱ ይችላል፤ይገባልም:: ከዚህ ሌላ መፈክር ወይም መንገድ የለም:: ድርጅቶች በመሀል ገብተው የሚበጠብጡትንን ሰርጎ ገቦች ሆኑ ወይም በአላዋቂ ሳሚነት ተገብዘውና አወቅን ብለው ድርጅቶችን በማጋጨትና በመከፋፈል ስራ የተሰማሩትን ሊያርቁ-- ሊቋቋሙ መቻል አለባቸው:

የድርጅቶችን ጥንካሬ ስንፈልግ ድርጅት ምን ፈይዶ ንቅናቄ እንጂ በሚል ያደናግረናል:: ቆራጥ ፀረ ወያኔ ትግል ስንል መደረክ መስርቶ ተወያይቶ በምርጫ መሳተፍ የሚል ፈሊጥ ይደነቅርብና ል:: የጠራ ያመረረ ፀረ ወያኔ ትግል ስንል እነ ስዬ--ገብሩ አስራትን ብትሞክሩስ ያስብላል:: ወያኔን አንገዳግዶ ወይም ጥሎ ሁሉን አቀፍ የሽግግር መንግስት ስንል ከወዲሁ በባዶ የስደት መንግስት ብሎ ማሾፊያ ሊያደርግን ይፈታተነናል:: ወዘተ:: ዛሬ የትግላችን መፈክር የወያኔን አገዛዝ አስወግዶ ዴሞክራሲያዊ ሽግግርን ማረጋገጥ የሚል ነው:: ሌሎች አደናቃፊ መፈክሮች ለወያኔ የሚጠቅሙ ወይም በወያኔ የተቀፈቀፉ ናቸው ብንል ስህተት አይሆንም:: ለዚህም ነው በመጀመሪያ ጥራትና ውስጣዊ ፅዳት አስፈላጊ የሚሆነው:: በሕዝብ ጎራ ብዙ የፖለቲካ ምስጦች ተሰማርተዋል:: በመጀመሪያ የላላውን መወጠር:: ያኔ ፤ያኔ ብቻ ነው ጠጣር ነኝ ያለው ሲወድቅ ለማየት የምንችለው::

ተቃዋሚ ኃይሎች ትግላቸውን ዛሬና በተጨባጩ መቃኘትና መምራት መቻል አለባቸው:: ይህም ማለት የአካባቢና ዓለም አቀፍ ሁኔታን በዕይታቸው አስገብተውና የኢትዮጵያንም ተጨባ ጭ ሁኔታ መርምረው አስፈላጊውንና ውጤታማ ሊሆን የሚችለውን ስልትና መርህ ገብር መያዝ አለባቸው ማለት ነው:: ትግል በገዋ--በአየር ላይ-- ወይም ባፈተተን ባሰኘን የሚካሄድ አይደለም ና ትግል እንዴት? ትግል ማን ላይ? ማን ወዳጅ ማን ጠላት? ብሎ ግልፅ ሆኖ መጀመር መካሄድ ያለበት ነው:: ይህ ተገቢውን ምላሽ ባለማግኘቱ በሕዝብ መተማመን ሲገባ ባዕዳን ላይ እምነትን መጫን፤ የአካባቢ ሁኔታን አጢኖ ማን በአንፃራዊ ደረጃ ወዳጅ ሊሆን መቻሉን መረዳት ሲቻል ሁሉንም ወይም መሆን የሌለባቸውን ሁሉ በጠላት መፈረጅ፤ በሀገራችን ላይ ያንዣበበውን የባዕድ አደጋ መረዳት አለመቻል በትግሉ ላይ ጉዳት አድርሷል:: ትላንት እነ እገሌና ድርጅቶች ከሻዕቢያ ጋር ተነጋገሩ በሚል ሲያወግዙና ፀያፍ ቃል ሲወረውሩ የነበሩ ዛሬ ከመ ቅፅበት --አለምንም ተሳስተን ነበር-- ሻዕቢያ ብቻ ሳይሆን የሶማሊያም አክራሪዎች ወዳጃችን ናቸው ሲሉ ሲደመጥ ምን ያህል ትግሉ በጥራዝ ነጠቆች ደፍርሶ እንደቆየ አመልካች ነው:: የሕዝብ ጎራ የዛሬን ተልዕኮና ዋና ስራ ከነገው ሳያደባልቅ ግን ከዕይታው ሳያርቅ በደረጃ በደረጃ በዋና ጠላት ላይ ያተኮረ ትግል ማካሄድ መቻል አለበት:: ይህን ካደረገ ዛሬ ሊደግፏቸው የሚፈልጓቸ ው ባዕዳን ሳይወዱ ሊደግፉ የሚችሉበት ሁኔታ ይፈጠራል እንጂ ነጋ ጠባ ሀገራችን ጠፋች እኮ ቢሏቸው ሀገራቸው ላልሆነችው ኢትዮጵያ የሚያዝኑበት ልብ ገና አልተተከለላቸውም::

በዲፕሎማሲውም ሆነ በሌላው መስክ ተቃዋሚ ኃይሎች ድክመታቸውን ለማስወገድ በሳልና ጠበቅ ያለ ስራ መስራታቸው ወሳኝ ነው:: ህጋዊ ነን ያሉትም ቢሆን በወያኔ ህግ የለምና ዛሬ ባይሆን ነገ ለሚመጣባቸው ጥቃት ከወዲሁ መዘጋጀትና መከላከል አለባቸው:: አለበለዚያ የሞኝ ገበሬ እርሻ በሰኔ ሆኖ ዳግም ጉዳትን መቀበል የግድ ይሆናል:: ዛሬ ወያኔ ሰርጎገቦቹን በየድርጅቱ አስገብቶ፤ ህብረተሰቡን በየደረጃው እያበጣበጠ መሆኑ መረሳት የለበትም:: ወረሩን ጨረሱን በሚል ወደ መርበትበት የሚገፋ ሁኔታ ባይሆንም ወያኔ ግን በዚህ የብጥበጣ ስራው የሚያግዙትን በስፋት ማሰማራቱና የሕዝብ ጎራ ደጋፊ መስለው ትግሉን በስልት የሚያጠቁ ስውር ቅጥረኞችን

*መትከሉ የሚታወቅ ነው:: ወያኔ ገዳይ ብሎ የሚያጓራውና መስመር ለቆ በመጮህ ለወያኔ ክሶች የሚያመቸውም በእርግጥም ወያኔ አለመሆኑ መጣራት አለበት:: ወደ መጡበት እንመልሳቸዋለን ብሎ ለእነ ስብሀት ነጋ ጥይት ያቀበለው መሰሪ ዛሬ የወያኔ ሎሌ ሆኖ እያየነው አይደል? በመሆኑ ም ድርጅቶች መላላታቸውን ለማስወገድ በአሰራርና በአደረጃጀት ጠበቅ ብለው፣ ለወያኔ ዝግ ሆነው፣ ከወያኔ አጫፋሪዎች ተለይተው፣ አዎ ወያኔና ደጋፊዎቹን ማኩረፍ ብቻ ሳይሆን ጠልተ ው መገኘት አለባቸው:: በዚህ ረገድም በወያኔ ዕቃዎችና የንግድ ተቋሞችና ከወያኔ አብረው በሚ ሰሩ ላይ ማዕቀብ ብለው በርካታ ድርጅቶች ማህበራት ከ1997 ጀምሮ የጠሩት ሙሉ ድጋፍን ሊያገኝ የሚገባው ነው:: ከወያኔ ጋር ግለሰቦችን የሚያያይዘው የቤትና መሬት መመራት፣የጥቅማ ጥቅምና ትርፍ እትብት ተበጥሶ መቃጠል አለበት ማለት ነው:: ለመጠናከር ከወያኔ መለያየትና በወያኔ አገዛዝ ላይ ጠላት ብሎ ማምረር ያስፈልገናል:: ሌላ አማራጭ የለውም::*

*ሕዝብንም በስፋትና በፅናት ሰብስበን ልናታግል የምንችለው ሕዝብን ሳናደናግር፣ ሲደግፈን ሸብረክ ደከም ጎንበስ ሳንል፣ ተንበርክኮ ትግልንና አንጃነትን ሳናቀነቅን፣ ሰፊውን ሕዝብ ሊስብ ሊያታግል የሚችል መርህ ግብር በወረቀት ብቻ ማስፈር ሳይሆን በተጨባጭ በመስዋዕትነት አርአያ ስንሆን፣ ዋይ ዋይታው ከወያኔም ጎራ እንዲቀልጥ ማድረግ ስንችልና በትግላችን ራሳችን ንም ኢትዮጵያን ስናስከብር ብቻ ነው:: ወያኔና የወያኔ ሎሌዎችን እያቀፍን፣ተለሳልሰን እየተቀበ ልን፣ ንዳን እንነዳ እያልን፣ ፀረ ወያኔዎችን በዚህም በዚያም እያዳከምን፣ ወያኔንም ባዕዳንንም መለመን የሰለጠነ ፖለቲካ ነው እያልን፣ የነገዪቷን ኢትዮጵያ ከቀድሞዋ ልናመሳስል እየጣርን፣ ወያኔያዊ መፈክርን እያስተጋባን፣ የትግሉ ቅደም ተከተል ጠፍቶን፣ ጠላትን ወዳጅ ብለን፣ ጋሪው ን ከፈረሱ በፊት እየገተርን፣ መና ከሰማይ እየጠበቅን፣ የድንጋይ ዳቦን ጊዜ እየናፈቅን፣ተግባር አልባ ሆነን ግን የታሪክ ቦታን ቅሚያ እያቀነቀንን፣ በታገለው ና በሚታገለው ላይ ነጋ ጠባ እየዘ መትን፣ በፀሎት ነፃነት በመጎንበስ ስርየት ብንል ኢትዮጵያችንን ከጥፋት አናድንም:: ዜጎች ደማቸውን ገብረው ቀናው መንገድ ይህ ነው ብለው ያሳዩንን የትግል ጎዳና ትተን በዘመናዊ ፈሪሳውያን፣ነቢያተ ሀሰትና ሐሳዊ መሲሆች በመደናገር በዚህም በዚያም እየተላተምን ግን ሁሌም ወኔ አልባ፣ተግባር ባዶ ሆነን ከተገኘን መጨረሻችን አሳዛኝ መሆኑ አይቀሬ ነው:: መላላት ብቻ ሳይሆን አላዋቂ እንደሰረው ሹራብ እንተረተራለን፣ እንፈታለን:: ይህን ደግሞ ማንም ሀገር ወዳድ ዜጋ ሊፈቅደው የሚችል ሊሆን አይገባም:: ጠጣሩ እንዲላላ የላላውን ወጥረን፣ተጠናክረን ና አይዞን በርታ ተባብለን ሀገራችንን ኢትዮጵያን ከጥፋት ማዳን መቻል አለብን::*

*የወያኔን አገዛዝ ለማስወገድ ትግላችን ይፋፋም!!*